# በቁማችሁ የሞታችሁ

እናት አገር ስትቆራረስ
ሕዝቧ መከራ ሲወርስ
ባሕል ታሪክ ሲጠፋ
ኢትዮጵያዊነት ሲንኳሰስ
የዘር ሀረግ ሲመዘዝ
በዘር ጥላቻ ሲታመስ
ይኸው 17 ዓመት ተገዛን
በዘረኛው ባምባገነኑ መለስ::

የወያኔ እድሜ የረዘመው
ሕዝቡ ወዶና ፈቅዶ አይደለም
አንዱ በጠባብነት ልክፍት
ከወንድሙ ጋር ሲላተም
የአገሩን ንዋይ በሽጠ
በዝርፊያ ለግል ጥቅም
ባድርባዩና ፈሪው
በገንዘብ የተገዛው ሆዳም
በሙያው የነገደ
አለሁ አለሁ ባይ አፈኛው
በደላላው በሕዝብ ስም
ወገን መስሎ በሚታየው
እያግባባ ከጠላት ጎራ
አታሎ አባብሎ በሚያስገባው
አገር ወዳዱን አዋርዶ
ሐቀኛ ልጆቹን ላስበላው
የሕዝብን ፍቅር በሽጠው
ለሆዱ በጥቅም ባደረው
በእንደነዚህ ዓይነቱ ስለሆነ
መዋጋትና ማጋለጥ እርሱን ነው::

እናንት በድሮ ዝና
በወገናችሁ የነገዳችሁ
ከሃዲ ባንዳ ሁሉ
በቁም ሞት የሞታችሁ
ያላችሁ መስሏችሁ ይሆናል
እውነቱን ልንገራችሁ
ሙትቾች አሳፋሪዎች
በቁም የተቀበራችሁ
ከሕዝብ የተለያችሁ
ወገናችሁን የከዳችሁ
ኢትዮጵያን ያደማችሁ
የጡት ነካሾች ናችሁ::
በወገን ደም ነገዳችሁ
የንጹሐን ደም ይፋረዳችሁ::
አጽማቸው አሾህ ሆኖ
በያለችሁበት ይውጋችሁ::
አይቀር ነገ ከነመለስ ጋር
መጠየቅና ለፍርድ መቅረባችሁ::

አገራችን ስትደማ
ሕዝባችን ሲሰቃይ
ፊታችሁን ያዞራችሁ
በድሃ ወገናችሁ ላይ
በሰኔ የተገደሉትን
እነዚያን ሰማዕታት
በኅዳር ለተጨፈጨፉት
ሕጻን፣ ወጣት፣ አዛውንት
ደማቸው ለሚጮኸው
የፍትሕ ያለህ ለሚለው
ምን ትላላችሁ እናንተ
አኮ መልሳችሁ ምንድነው?
በሚኞቹ ታመካኙ ይሆን
ጥፋቱ የእነርሱ ነው
ትከሷቸው ይሆን ብላችሁ
የመንገድ ነውጠኞች ናቸው
እኮ አይታችሁ እንዳላየ
ሰምታችሁ እንዳልሰማችሁ
ከቶ ምንድነው መልሳችሁ
ሆዳችሁ በልጦባችሁ
ሁሉንም ነገር ክዳችሁ
"መቻቻል" "እርቅ" እያላችሁ
የወገናችሁን ደም የረገጣችሁ
እናንተ የተረገማችሁ
ያላችሁ መስሏችሁ ይሆናል
ቆየ እኮ በቁም ከሞታችሁ::

የሕዝብን ትግል ከድታችሁ
ምድረ የቃሊቲ ባንዳ
ቃላችሁን ያጠፋችሁ
የተገዛችሁ በምንዳ
ጥቅምና ፍርፋሪ ፈልጋችሁ
ገብታችሁ ከጠላት ጓዳ
በአፈንጋጮች ሴራና ዱለታ
የሕዝብ ትግል ሲጎዳ
እናንተ አያድርገኝ ያኔ
የሕዝብ ቁጣ እንደቦንብ ሲፈነዳ::
የእድሜ ባለጸጋ ምሑር
ለእውነት መቆም አቅቶት
አቅቶት ሲዘባርቅ ሰማነው
ፈጠነችን ሲለን ተከተሏት
እንዲህም አድርጎ ምክር የለ
በችግር ላይ ችግር ሊያመጣ
እርሱው የበጠበጠው መርዝ
ያመጣብን መዘዝ ጣጣ
ግራ ሲያጋባን ሰንብቶ
መጨረሻው እውነቱ ወጣ::
ሕዝብ ጠላቱን አንገዋሎ
አፈንጋጩን አጣጥሎ
ከወያኔ ጋር ጠቅልሎ
እናንት ወጊዱልን ቶሎ
ሲል የጠራ አቂሙን ተናግሯል
ከዳር እስከ ዳር ሲመክር ውሎ
ቅንጅት አንድ ነው
መሪውም ኃይሉ ሻውል ብሎ::

ከኃይለ ልዑል ግርማ